6/9/2016



# የቅኔ መግቢያ

| ጳውሎስ ብርሃኔ/የቅኔ መምህር/

## ማውጫ

ማውጫ ........ i

የአዘጋጁ መግለጫ ........ 1

1.ቅኔ በብሉይ ኪዳን ........ 1

2. ቅኔ በሐዲስ ኪዳን (ወንጌል) ........ 2

3. ቅኔ በሃይማኖተ አበው (በሊቃውንት) ........ 2

4. የቅኔ ትምህርት ጠቀሜታዎች ........ 3

5. የቅኔ ደረጃዎች ........ 3

6. ቅኔ ለመቀኘት ወይም ለመዝረፍ ቅድመ ኹኔታዎች ........ 3

7. የቅኔ የትምህርት ዘዴዎች ........ 4

8.የቅኔ ቤት አወቃቀር ........ 5

9.የቅኔ የትምህርት ኺደት ........ 5

10.ቅኔ በቤተ ክርስቲያን ያለው የአገልግሎት ድርሻ ........ 6

## የአዘጋጁ መግለጫ

**ስም ጳውሎስ ብርሃኔ/የቅኔ መምህር/**

**የትምህርት ደረጃ የቅኔ መምህር**

**ቅኔ ያስተማሩኝ መምህራን ዝርዝር**

**ስም ቦታ**

- **መ/ለይኩን………………/ምዕራብ ጎጃም ፤ጫፍቃት**
- **መ/ተከሥተ ብርሃን………/ምዕራብ ጎጃም ፤ዋድ ኢየሱስ**
- **መ/መክብብ………………/ምሥራቅ ጎጃም ፤ሉማሜ**
- **መ/መርሐ ጽድቅ/ናቄ……ምሥራቅ ጎጃም ፤ ደጀን**
- **መ/አክሊሉ………………ምሥራቅ ጎጃም. ፤ አማኑኤል**
- **መ/ገብረ ሕይወት ፈንታሁን…አዲስ አበባ ፤ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ**
- **ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው……ምዕራብ ጎጃም ፤ጨጎዴ**

## 1.ቅኔ በብሉይ ኪዳን

**በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ቤት /ስንኝ/ አልባ ቅኔዎች**

- **ወእምዕፅሰ ዘያርኢ ወያሌቡ ሠናየ ወእኩየ ኢትብላዕ እምኔሁ እስመ በዕለተ ትበልዕ እምኔሁ ሞተ ትመውት** (ዘፍ2 ፡17)
- **ወይቤ አዳም ሶቤሃ ዛቲ ዐፅም እምአፅምየ ወሥጋ እምሥጋየ ለትኩነኒ ብእሲትየ እስመ እምታ ወጽአት ይእቲ**….(ዘፍ2 ፡23-25)
- **አሥዋክ ወአሜከላ ይብቊልከ ወብላዕ ሣዕረ ገዳሞ**……...(ዘፍ3 ፡18-19)
- **ወሖሩ ዕፀው ያንግሡ ሎሙ ንጉሠ ወይቤልዋ ለዕፀ ዘይት ንዒ ንግሢ ለነ**.....(መሳፍ 9 ፡6-20)
- **ሠረገላቲሁ ለእግዚአብሔር ምልፊተ አዕላፍ ፍሡሐን** (መዝ 67 ፡17)
- **ወፍናዊሁ ለሞት ዘእግዚአብሔር ውእቱ** (መዝ 67 ፡20)

## 2. ቅኔ በሐዲስ ኪዳን (ወንጌል)

- ወይብል ጺሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ወርቱዐ ግበሩ መጽያሕቶ ፡ ፡(ማቴ 3 ፡3)
- ግበሩኬ እንከ ፍሬ ሠናየ ዘይደልወክሙ ለንስሓ…..(ማቴ 3 ፡8-11)
- ወአንተሰ ሶበ ትገብር ምጽዋተ ኢታእምር ፀጋምከ ዘትገብር የማንከ (ማቴ 6 ፡3-6)
- ኢይክል አሐዱ ገብር ተቀንዮ ለክልኤ አጋዕዝት (ማቴ ፡624)
- ተዐቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት እለ ይመጽኡ ኀቤክሙ በአልባሰ አባግዕ (ማቴ 7 ፡15-19)
- ኵሉኬ ዘይሰምዕ ዘንተ ቃልየ ወይገብሮ ይመስል ብእሴ ጠቢበ ዘሐነፀ ቤቶ ዲበ ኰኵሕ ዘንሙ ዝናማት ወውኅዙ ወሐይዝት ወነፍሑ ነፋሳት ወግፍዕዎ ለውእቱ ቤት ወኢወድቀ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ….. (ማቴ24 ፡27)
- ወእምበለስ አእምሩ አምሳሊሁ እምከመ ኮነ አጽቃ ድኩመ ወቆጽላ ለምለመ ተአምሩ ከመ ቀርበ ማእረር (ማቴ 24 ፡32)
- ወለጸጉርሰ ይለፅፍዎ ወእመአኮ ይቀርጽዎ ወለአጽፋርሂ ይመትርዎሙ ወይሠርጹ ዳግመ… .(ሃ.አ ዘኢጵፋንዮስ ምዕ 58 ፡2-18)

## 3. ቅኔ በሃይማኖተ አበው (በሊቃውንት)

- ወእምዝ አስተቀጸለነ ጌራ መንግሥት ዘለዓለም ዘሥርግው በእሉ አዕናቍ ክብር (ሃ.አ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ምዕ 36 ፡3)
- ንሕነሰ አብደርነ ሞተ እምሕይወት ወኀሳረ እምተድላ በፈቃድነ ወበተወክፎተ አስፍጦተ ፀርነ (ሃ.አ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ምዕ 36 ፡14)
- ወአርኀወ ለነ ኆኅተ ንስሓ ወወሀበነ መባሕተ ከመ ንጸውዖ ለአብ (ሃ.አ ጎርጎ ዘኑሲስ 36 ፡30)
- ወውእቱ በግዐ መሥዋዕት ወውእቱ ካህን ሠዋዒ ወውእቱ ተወካፌ መሥዋዕት(ሃ.አ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ምዕ 36 ፡36)
- ወመጸሕፍት ቅዱሳት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ይቤሉ ከመ ውእቱ ሐመ በሥጋ(ሃ.አ.ዘቄርሎስ 78 ፡67)
- … በከመ መሀሩነ ሐዋርያት እንዘ ይብሉ አብ ፀሐይ ፣ ወልድ ፀሐይ ፣ መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ ….. (አባ ሕርያቆስ)

## 4. የቅኔ ትምህርት ጠቀሜታዎች

የግእዝ ቋንቋን ለማወቅ

በግእዝ የተጻፉ መጻሕፍትን ለመተርጎም

በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ንባባትን ቃላቶችን ፣አገባቦችን ፣ግሦችን ፣ የንባብ ስልቶችን ጠብቆ ለማንበብና ለመረዳት

ለፍልስፍና ጥበብ

ለምርምር ሥራዎች ወዘተ

## 5. የቅኔ ደረጃዎች

1. ጉባኤ ቃና
2. ዘአምላኪየ
3. ሚ በዝኁ
4. ዋዜማ/ዋይ ዜማ
5. ሥላሴ
6. ዘይእዜ
7. መወድስ
8. በተጓዳኝ ክብር ይእቲና ዕጣነ ሞገር

## 6. ቅኔ ለመቀኘት ወይም ለመዝረፍ ቅድመ ኹኔታዎች

የዕለቱ ታሪክ ዋና ዋና ነጥቦች

ለምሳሌ ፡- ዛሬ 9/6/2016 ዓ.ም ቅኔ የሚያስነግሩ ኩነቶች

1. ቶማስ ዘመራስ (ወርኃዊ)

የቶማስ እግሮቹ ፣እጆቹ ፣እጣቶቹ ፣ከንፈሮቹ መቆረጣቸው

ቶማስ በቅርጫት ኹኖ በአኽያ እየተጫነ ወንጌል ማስተማሩ

2. ስምዖን (ዐመታዊ) የእሑድ መዝሙር እስካልሻረው ድረስ ያስነግራል

ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ መግባቱ

ስምዖን (አረጋዊ) ጌታን መታቀፉ

ስምዖን ጌታነን ሲታቀፍ መታደሱ/ወጣት መኾኑ

የስምዖን ዐይኖች መብራታቸው

- ወርቅ የሚኾኑ ቃላት (ለቶማስ)

ቶማስ ፣አእጋረ ቶማስ ፣አእዳወ ቶማስ ፣ከናፍረ ቶማስ

ተጽዕኖ አድግ ፣አጽፈሬዳ(ቅርጫት) ፣

ሰይፍ ፣ምትረት ፣ሥቃይ ፣ገድል/ተጋድሎ/

ሃይማኖት ፣ሰብከተ ወንጌል ፣ትምህርተ ወንጌል…

- ወርቅ የሚኾኑ ቃላት (ለስምዖን)

ስምዖን ፣ተሐቅፎተ ወልድ(ጌታ) ፣ ሐቂፈ ስምዖን ፣

ሕዳሴ ስምዖን/ተሐድሶ ስምዖን ፣

አዕይንተ ስምዖን ፣ብርሃነ አዕይንት ዘስምዖን

በአተ ቤተ መቅደስ ዘወልድ

## 7. የቅኔ የትምህርት ዘዴዎች

1. ንባብ/ዘር ፡- የቅኔውን ንባብ ማስቀመጥ
2. ፍቺ ፡- በንባብ የተቀመጠውን ቅኔ መፍታት
3. ርቃቄ ፡- የቅኔውን ሠምና ወርቅ ለይቶ ማመስጠር

3.1. ሠም ፡- የቅነው ሠማዊ መልእክትን ለይቶ ማብራራት

3.2. ወርቅ ፡- የቅኔውን ወርቃዊ መልእክት ለይቶ ማብራራት

4. ሙያ ፡- በቅኔው ውስጥ ያሉ አገባቦችን ፣ስሞችን ፣ባለቤቶችን ፣ ግሶችን…ሙያ ማደል
5. የቅኔው ዋናው መልእክት ፡- የቅኔው ሃይማኖታዊ ፣ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ መልእክት
6. የቅኔው መንገድ ፡- የቅኔውን መንገድ ስያሜ ማውጣት
7. የቅኔው ዘይቤ ፡- የቅኔውን የዘይቤ ዐይነት መለየት

## 8. የቅኔ ቤት አወቃቀር

### ❖ በቅኔ ቤት ያሉ የሥልጣን ተዋረድ

- ☞ የቅኔ መምህር
- ☞ የቅኔ ዘራፊ
- ☞ የቅኔ አስነጋሪ
- ☞ አንደኛ/ዋና/ አስቀጻዮች
- ☞ ኹለተኛ አስቀጻዮች
- ☞ ሦስተኛ አስቀጻዮች
- ☞ ተማሪዎች

## 9. የቅኔ የትምህርት ኺደት

### ❖ የመምህሩ ድርሻ

- ☞ ግስ መግሰስ/ማውረድ
- ☞ ታሪክ መተረክ/የወር ፤የዐመት)
- ☞ ቅኔ መዝረፍ
- ☞ የተዘረፈውን ቅኔ ማስቀጸል/ፍቺ ፤ርቃቂ ፤ሙያ/
- ☞ ቅኔ ማስነገር/ማረም

### ❖ የተማሪው ድርሻ

- ☞ ግስ ማጥናት
- ☞ የተዘረፈውን ቅኔ መቀጸል
- ☞ ቅኔ ቆጥሮ መንገር
- ☞ የታረመለትን ቅኔ መቀጸል

## 10.ቅኔ በቤተ ክርስቲያን ያለው የአገልግሎት ድርሻ

ቅኔ በዓይነቱ በኢትዮጵያ ኦርዶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቅዱስ ያሬድ የዜማ አገልገሎት ጋር በተለያዩ በዓላትና ዕለታት ፣ ማለትም ፡-

1. በዕለተ ሰንበት/እሑድ/
2. በክብረ በዓል ዋዜማ/በዋይዜማ ቁመት/ማኅሌት/ ጊዜ
3. በክብረ በዓል ዕለት ፡- የክብረ በዓል ማኅሌትና የአርያም ቁመት ጊዜ
4. በክብረ በዓል ዕለት ፡- የክብረ በዓል ማኅሌትና የዐቢይ ስብሐተ ነግህ ቁመት
5. የዘወትር ስብሐተ ነግህ ቁመት ጊዜ ሰፊውን አገልግሎት ቦታ ይዞ ይገኛል ፡ ፡

ስለሆነም እንዴት በአገልግሎት ላይ እንደሚሰጥ/እንደሚውል) ከዚህ በታች ይገለጻል ፡ ፡

### 1. በአርባዕት መወድስ ቁመትና በዋይዜማ የማኅሌት ቁመት የሚደርሱ ቅኔዎች

1..1 በአርባዕት መወድስ ቁመት ጊዜ የሚደርሱ ቅኔዎችና መዝሙራተ ዳዊት

| ተ.ቁ | የሚደርሱ ቅኔዎች | መዝሙራተ ዳዊት ወነቢያት |
|---|---|---|
| 1 | ግእዝ ጉባኤ ቃና | ○ ቃልየ አጽም እግዚኦ ወለቡ..<br>○ ከመ ያፈቅር ኀየል ኀበ አንቅዕተ ማያት<br>○ ዐቢይ እግዚአብሔር ወብዙኀ አኰቴቱ… |
| 2 | ሚ በዝኁ ቅኔ | ❖ እግዚኦ ሚ በዝኁ እለ ይሳቅዩኒ..<br>❖ ብፁዕ ዘይሌቡ… |
| 3 | መወድስ ቅኔ | ፍታሕ ሊተ እግዚኦ |
| 4 | 2 ቤት(አጭር) ዋይዜማ ቅኔ | ጉሣዕ ልብየ… |
| 5 | ኩልክሙ መወድስ ቅኔ<br>(አጭር / ረጅም ) | ○ ኩልክ አሕዛብ…<br>○ ጥፍሑ እደዊክሙ… |
| 6 | ሣልስ ቅኔ | ተሠሀለኒ እግዚኦ በከመ ዕበየ ሣህልከ… |
| 7 | ዋይዜማ ቅኔ | ❖ ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር…<br>❖ እግዚአብሔር ነግሠ… |

1.2. በወይዜማ ቁመት ጊዜ የሚደርሱ ቅኔዎች

| ተ.ቁ | የሚደርሱ ቅኔዎች | መዝሙራተ ዳዊት ወነቢያት |
|---|---|---|
| 1 | ዋይዜማ ቅኔ | ❖ ለእግዚአብሔር ምድር በምልኣ<br>❖ እግዚብሔር ነግሠ<br>❖ እግዚኦ ጸራሕኩ ኀቤከ…. |
| 2 | ሥላሴ ቅኔ | ○ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ<br>○ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላ አበዊነ(ዕዝል ከሆነ) |
| 3 | ዘይእዜ ቅኔ | ✓ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ ይትባረክ እግዚብሔር አምላከ አበዊነ<br>✓ (ድጓው(ዜማው) ግእዝ ከሆነ) |

2. **በአርያምና በዐቢይ ስብሐተ ነግህ ቁመት ጊዜ የሚደረሱ ቅኔዎች**

2.1. በአርያም ቁመት ጊዜ የሚደረሱ ቅኔዎች

| ተ.ቁ | የሚደርሱ ቅኔዎች | መዝሙራት ዳዊት ወነቢያት |
|---|---|---|
| 1 | ሚ በዝኁ | ናሁ ይባርክ |
| 2 | ሥላሴ ቅኔ | ከሦስቱ በስተቀር በአጠቃላይ መዝሙራተ ነቢያት ማለትም ፡-<br>❖ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ፣<br>❖ አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ ፣<br>❖ እስመ እሳት ትነድድ … |

2.2. በዐቢይ ስብሐተ ነግህ ቁመት ጊዜ የሚደረሱ ቅኔያት

| ተ.ቁ | የሚደረሱ ቅኔዎች | መዝሙራተ ዳዊት ወነቢያት |
|---|---|---|
| 1 | ዕዝል ጉባኤ ቃና ቅኔ<br>(ዓርብና ረቡዕ ብቻ) | ❖ አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ<br>❖ ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር<br>❖ ቃልየ አጽዕ እግዚኦ ወለቡ ጽራሕየ<br>❖ ለከ ይደሉ እግዚኦ ስብሐት በጽዮን…. |
| 2 | ዘአምላኪየ ቅኔ<br>(ዓርብና ረቡዕ በስተቀር) | ○ አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ<br>○ ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር<br>○ ቃልየ አጽዕ እግዚኦ ወለቡ ጽራሕየ<br>○ ለከ ይደሉ እግዚኦ ስብሐት በጽዮን…. |
| 3 | ሥላሴ ቅኔ | ❖ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እምሰማያት<br>❖ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ<br>❖ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ<br>❖ ጸሎተ ስምየን ይእዜ ትስእሮ ለገብርከ (ድጓው ዕዝል ከሆነ) |
| 4 | ዘይእዜ ቅኔ | ጸሎተ ስምየን ይእዜ ትሥእሮ ለገብርከ (ድጓው ዜማው ግእዝ ከሆነ) |

3. **በቅዳሴ ጊዜ የሚደረሱ ቅኔዎች**

በቅዳሴ ጊዜ ቅኔዎች የሚደረሱት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሥርዐታተ ማኅሌት ውስጥ አንዱ ሲፈጸም ብቻ ነው ፡፡

1. ግእዝ/ዕዝል ክብር ይእቲ ቅኔ ከቁርባን በፊት ሊቀ ዲያቆኑ ጸልዩ ባለጊዜ በጥንተ መሪ/በተጋባዥ ይደረጋል ፡፡
2. ግእዝ (ዕዝል) ዕጣነ ሞገረ ቅኔ የክብር ይእቲ ሥርዐተ ማኅሌት አልቆ ዝማሬ ከተቃኘ በኋላ በባለ ክብር ይእቲው ይደረሳል

አነሳስቶ ያስጀመረን አስጀምሮ ያስፈጸመን የአባቶቻችን ነቢያት ፣ሐዋርያት ፣ጻድቃን ፣ሰማዕት አምላክ የተመሰገነ ይኹን የሰማነውን በእዝነ ልቡናችን ያሳድርብን

አቡነ ዘበሰማያት